አዋጅ ቁጥር ----/2019

የፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ስያሜ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማትን አደረጃጀት ተቋማቱ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል፣ ከሌሎች ተቋማት ሥልጣንና ተግባር ጋር የተጣጣመ፣ የሀብት ብክነትን የሚቀንስ፣ ውጤታማነትን የሚያበረታታ እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማት የታላቁ የመደመር ስትራቴጂ ለማስፈጸም በሚያስችል መዋቅር ማደራጀት በማስፈለጉ፤

የአስፈጻሚ አካላትን ስያሜ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለአገልግሎት ተጠቃሚ ማህበረሰብ ግልጽ፣ ተገማች እና በቀላሉ እንዲታወቅ በሚያስችል መልኩ መደንገግ እንዲሁም ተቋማቱ ከተቋቋሙበት ዓላማ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአስፈጻሚ ተቋማትን ስያሜ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር በጥናት ላይ በመመስረት ዘላቂነት ያለው እንዲሁም ከማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የቴክኖሎጂ ለውጥ ጋር ተጣጥመው እንዲቀጥሉ የሚያስችል ሥርዓት በሕግ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 56 መሠረት የፌዴራል መንግሥት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለውን የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት በሕግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት ስያሜ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ------/ 2019" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የኃረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1) **"ሕገ-መንግሥት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው፡፡

2) **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፡፡

3) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴት ፆታን ይጨምራል።

ክፍል ሁለት

ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት

3. የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 74 የተመለከተው ነው።

4. የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 75 የተመለከተው ነው።

5. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 77 የተመለከተው ነው።

6. የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ለ) ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 የተመለከቱትን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የሚመሩ ሚኒስትሮች፣ እና

መ) በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣኖች።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) ስር የተመለከተ ማንኛውም ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ዴኤታ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፤ ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል።

7. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት፦

ሀ) ሥራውን በአግባቡ ለማካሄድ አስፈላጊው የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤

ለ) በውስጥ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤

ሐ) ስብሰባ ላይ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፤

መ) የሚያስተላልፈው ውሳኔ በሙሉ ድምጽ ይሆናል፤ በሙሉ ድምፅ መወሰን ካልተቻለ በአብላጫ ድምጽ ይወሰናል፤ የተሰጠው ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያለበት ወገን ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

2) ጠቅላይ ሚኒስትሩ፦

ሀ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

ለ) የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

ሐ) ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል፤

8. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች</u>

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል፡፡

2) የቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>የፌዴራል አስፈጻሚ አካላት ስያሜ</u>

9. <u>ስለ ሚኒስቴር</u>

በሚከተለው አግባብ የሚቋቋም አስፈጻሚ ተቋም በሚኒስቴርነት ይሰየማል፡-

1) በዋናነት ሥራውን በሚያከናውንበት ዘርፍ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ፕሮግራም የሚቀርፅ፤ ሲፀድቁም በበላይነት ተፈፃሚነታቸውን የሚመራና የሚያስተባብር፤

2) በሚሰማራበት ዘርፍ በሚመለከተው አካል የሚወጡ ስታንዳርዶችን የሚያስፈፅም ወይም መተግበራቸውን የሚያረጋግጥ፣ የቁጥጥር ሥራዎችን የሚያከናውን እንደአስፈላጊነቱ ፈቃድ የሚሰጥ፣ አቅም በመገንባት እንዲሁም በተጨባጭ ፕሮግራምን ወደ ፕሮጀክትነት በመቀየር የቀን ተቀን ሥራዎችን የሚያከናውን እና አገልግሎት የሚሰጥ፤

3) ተጠሪ ለሆነለት ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ላለው ለሌላ የፌዴራል ወይም የክልል ተቋም ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በከፊል በውክልና የሚሰጥ፡፡

10. <u>ስለ ኮሚሽን</u>

በሚከተለው አግባብ የሚቋቋም አስፈጻሚ ተቋም በኮሚሽንነት ይሰየማል፡-

1) ለተወካዮች ምክር ቤት፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ወይም ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ተጠሪ የሚሆን፤

2) የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን ሥራ የሚያቀናጅና የሚያስተባብር፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ የሚቀርፅ እንዲሁም አፈፃፀሙን በበላይነት የሚመራ፤

3) እንደአግባቡ ዘላቂ ለሆነ ወይም በአንዳንድ ሁኔታ በጊዜያዊነት አንገብጋቢ ለሆኑ ጉዳዮች ሊቋቋም የሚችል፡፡

11. <u>ስለ ባለሥልጣን</u>

በሚከተለው አግባብ የሚቋቋም አስፈጻሚ ተቋም በባለሥልጣንነት ይሰየማል፡-

1) በሚመለከተው አካል የሚወጡ የቁጥጥር ደረጃዎችን የሚያስፈፅም ወይም መተግበራቸውን የሚያረጋግጥ፣ የቁጥጥር ሥራዎችን የሚያከናውን ፤

2) ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ተጠሪ የሚሆን ወይም ተጠሪ ከሆነለት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሥራ ጋር የጥቅም ግጭት ይኖራል ተብሎ ሲገመት ለጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ለሌላ የመንግስት አካል ተጠሪ የሚሆን፤

3) በዋናነት በተሰጠው የዘርፍ ሥራ በሚመለከተው አካል የሚወጡ ስታንዳርዶችን የሚያስፈፅም ወይም መተግበራቸውን የሚያረጋግጥ፣ የቁጥጥር ሥራዎችን የሚያከናውን፤

4) ፍቃድ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲኖሩ ፍቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ሥራን የሚያከናውን፡፡

12. <u>ስለ አስተዳደር ወይም ልማት</u>

በሚከተለው አግባብ የሚቋቋም አስፈጻሚ ተቋም በአስተዳደርነት ወይም በልማትነት ይሰየማል፡-

1) ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ሥልጣን ወደታች ለማውረድ በዋናነት የሚከናወን የመሠረተ-ልማት ግንባታ፣ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የመሠረተ-ልማት ጥገና እና አስተዳደርን በመደበኛነት የሚያከናውን እና ሥራዎችን በበላይነት የሚመራ፤

2) የመሠረተ-ልማት ግንባታ፣ ጥገና፣ አገልግሎት አሰጣጥ እና አስተዳደር ለማከናወን ሌላ የመንግሥት ልማት ድርጅትን ወይም የግል ድርጅትን በመጠቀም የተሰጠውን ሃላፊነት የሚወጣ፡፡

13. <u>ስለ አገልግሎት</u>

አንድ ተቋም በዋናነት ለመንግሥት አካላት አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን በማዕከል ደረጃ ለመስጠት የሚቋቋም ወይም በዋናነት ለዜጎች አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በአገልግሎትነት ይሰየማል፡፡

14. <u>ስለ ጽሕፈት ቤት</u>

አንድ ተቋም ልዩ ትኩረት የሚፈልግ ተግባርን ለማከናወን ወይም የተለያዩ ተቋማትን ለማስተባበር ለጊዜያዊ ወይም ለቋሚ ዓላማ በልዩ ሁኔታ የሚቋቋም ከሆነ በጽሕፈት ቤትነት ይሰየማል፡፡

15. <u>ኢንስቲቲዩት</u>

አንድ ተቋም ተጠሪነቱ እንደተሰማራበት የሥራ ዘርፍ አግባብ ላለው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ወይም ሌላ መሥሪያ ቤት የሆነ፣ በሥልጠና፣ በጥናትና ምርምር እና በማማከር አገልግሎት ላይ የሚያተኩር እና በተቋቋመበት ዘርፍ ልምድና ሙያዊ ብቃት ያለው አመራር ያለው ከሆነ በኢንስቲቲዩትነት ይሰየማል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ስለሚኒስቴሮች መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ሥልጣንና ተግባር</u>

<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

<u>ስለሚኒስቴሮች መቋቋምና የሚኒስትሮች ተጠሪነት</u>

16. <u>የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች መቋቋም</u>

የሚከተሉት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1) የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር፣

2) የመከላከያ ሚኒስቴር፣

3) የማዕድን ሚኒስቴር፣

4) የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣

5) የሰላም ሚኒስቴር፣

6) የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

7) የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣

8) የብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር

9) የትምህርት ሚኒስቴር፣

10) የሎጅስቲክስ ሚኒስቴር፣

11) የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣

12) የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣

13) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣

14) የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር፣

15) የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር፣

16) የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣

17) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

18) የገቢዎች ሚኒስቴር፣

19) የገንዘብ ሚኒስቴር፣

20) የግብርና ሚኒስቴር፣

21) የጤና ሚኒስቴር፣

22) የፍትሕ ሚኒስቴር፣

17. <u>የሚኒስትሮች ተጠሪነትና ኃላፊነት</u>

እያንዳንዱ ሚኒስትር፡-

1) ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል፤

2) የሚመራውን ሚኒስቴር ይወክላል፣ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ያውላል፤

3) ለሚኒስቴሩ በተፈቀደው በጀትና የልማት እቅድና ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ መሆኑን ያረጋግጣል፤

4) በሚኒስቴሩ ውስጥ የአመራር አተገባበር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል።

18. <u>የሚኒስትር ዴኤታዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት</u>

1) የእያንዳንዱ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ የተመደበበትን ዘርፍ ተግባራት ያከናውናል፡፡

2) ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ሚኒስትር ዴኤታው ተክቶት ይሠራል፤ ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ ተክቶት ይሠራል።

3) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 እና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ቢኖሩም የሚኒስትሮችና የሚኒስትር ዴኤታዎች የወልና የተናጠል ተግባርና ኃላፊነትን በተመለከተ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ ይችላል።

ንዑስ ክፍል ሁለት

የሚኒስቴሮች ሥልጣንና ተግባራት

19. የሚኒስቴሮች የወል ሥልጣንና ተግባራት

እያንዳንዱ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅና በሌላ ሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መስክ፡-

1) የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤

2) በጥናት ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ፕሮግራሞችን ያመነጫል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

3) የፌዴራል መንግሥት ሕጎችን ያመነጫል፤ ሲፀድቅም ያስፈጽማል፤

4) ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን በሥራ ላይ ለማዋል ከሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት ጋር አስፈላጊውን ቅንጅት በመፍጠር ይሠራል፤

5) የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ቅድሚያ ከሚሰጣቸው የኢንቨስትመንትና ሌሎች የመንግሥት የልማት ፖሊሲዎችና ዕቅዶች ጋር በማጣጣም ያከናውናል፤

6) እንዳስፈላጊነቱ የግል ዘርፉንና ሰፊ የማኅበረሰብ ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

7) ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

8) የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

9) እንዳስፈላጊነቱ ለክልሎች ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤ የተለየ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፤

10) ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

11) በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም ዓቀፍስምምነቶችን ይፈራረማል፤

12) የሚያመነጫቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶች፣ የሕፃናት፣ የወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

13) የሰብዓዊ መብቶችን ያከብራል፣ ያስከብራል፤

14) ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

15) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ የፌዴራል ወይም የክልል አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

20. <u>የመስኖና የቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የመስኖና የቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የመስኖ ልማት፣ የቆላማ፣ እና ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች እና የአርብቶ አደር ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2) የመስኖ ልማት እንዲስፋፋና ሽፋኑ እንዲያድግ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
3) በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጥናት የተለዩ የሀገሪቱን የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር የውሃ ሃብት ለመስኖ ልማት የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
4) የመስኖ ልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤
5) የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ምርታማነት በሚያሳድጉ ወቅታዊ ቴክኖሎጂዎች እንዲደገፉና ውሃ ቆጣቢ አሠራር እንዲከተሉ ያበረታታል፤
6) በተፋሰሶች ውስጥ የሚደረጉ የመስኖ ማስፋፋት ሥራዎችን ለመደገፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤
7) የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ፋይናንስ እንዲያገኙ በተለያዩ ዘዴዎች ያስተዋውቃል፤ ሕግን መሠረት በማድረግ ባለሃብቶች ማትጊያ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
8) በመስኖ ዘርፍ በመንግሥትና በግል አጋርነት የሚከናወኑ የመስኖ ልማት ዘርፎችን በመለየት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
9) በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢው ህብረተሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
10) በፌዴራል መንግሥት የተገነቡ የመስኖ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን ያስተዳድራል፤
11) ለክልሎች መስኖ ልማት ተቋማት አቅም ግንባታ አስፈላጊውን የሙያና ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ ሀገራዊ የመስኖ ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞችን በየደረጃው ተፈፃሚ ለማድረግ በክልሎች መከናወን ያለባቸው የመስኖ ልማት ተግባራትን በመለየት የጋራ መግባባት ተደርሶባቸው በየደረጃው ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤
12) የመስኖ ልማት መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ይዘረጋል፤
13) በቆላ አካባቢዎች ያለውን የመስኖ ልማት አቅም ለመለየት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤ የአካባቢውን የግብርና መሬት ለማልማት የሚያስችል የመስኖ ልማት ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤
14) ከግብርና እና ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ውሃን ማዕከል ያደረጉ የመስኖና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
15) በአርብቶ አደር አካባቢ ለእንስሳት ሀብት ልማት አስፈላጊ የሆኑ የውሃ ተፋሰስ ሥራዎች፣ መሠረተ-ልማትና የመስኖ ባንኮች መስፋፋታቸውን ይከታተላል፤
16) አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮችን የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስተባብራል፡፡
17) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል።

21. <u>የመከላከያ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የመከላከያ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሀገር መከላከያ ሠራዊት ግንባታን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2) አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሀገሪቱን የግዛት ሉዓላዊነት ያስከብራል፤ ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋና ከጥቃት ይከላከላል፤
3) ሀገር መከላከልን በሚመለከት አግባብ ያላቸውን የፌዴራልና የክልል አካላት ያስተባብራል፣ በመተባበር ይሠራል፤
4) መከላከያ ሠራዊት ያቋቁማል፣ ያስታጥቃል፣ ይቆጣጠራል፣ የውጊያ ብቃቱን ያረጋግጣል፤
5) የመከላከያ ሠራዊት ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲደራጁ ያደርጋል፤
6) የጦር ሠፈሮችንና ለሠራዊቱ የሚያስፈልጉትን የመኖሪያ ሠፈሮች ይሠራል፣ ያሠራል፤
7) የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽዖ ያካተተ መሆኑን ያረጋግጣል፤
8) የመከላከያ ሠራዊት ተግባር ለሕገ-መንግሥቱ ተገዢ እና ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ማከናወኑን ያረጋግጣል፤
9) በሕገ መንግሥቱና አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት በሚሰጥ ስምሪት በክልሎች የሕግ የማስከበር ሥራ ይሰራል፤ ሰላምና መረጋጋትን ያሰፍናል፤
10) በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤
11) የክተት አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ በሀገር ውስጥ የሚገኝ ሀብት በተቀናጀ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ እያጠና ያስወስናል፤ ኅብረተሰቡ ከጠላት ጥቃት ራሱን የሚከላከልበትን ዕቅድ ያወጣል፣ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
12) በጦርነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመከላከያ ሠራዊትን የሚቀላቀል፣ እንዲሁም ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ እገዛ የሚያደርግ ብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ያደራጃል፤
13) የሽምቅ ውጊያንና ሽብርተኝነትን ይከላከላል፤
14) ሀገሪቱ የሚቀርብላትን ዓለም ዓቀፍ የሰላም ማስከበር ጥሪ በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የሰላም አስከባሪ ኃይል ያደራጃል፣ ያሰማራል፤
15) የሠራዊቱ አባላት በሰላም ጊዜ በሀገሪቱ የልማት ሥራዎች እንዲሳተፉ ያደርጋል፤
16) የመከላከያ ተቋማት በሰላም ጊዜ የሚኖራቸውን የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ትርፍ አቅም በመጠቀም የሚያገኘውን ገቢ፣ ለመከላከያ ጠቀሜታ የማያስፈልጉ ንብረቶችን በማስወገድ የሚገኘውን ገቢ እና በተቆጣጣሪ ባለሥልጣንነት ከሚመራቸው ድርጅቶች የሚያገኘውን የትርፍ ድርሻ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን እያስፈቀደ ለሀገር መከላከያ አቅም ግንባታ እንዲውል ያደርጋል፤
17) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(አ) ስር የተመለከተው ገንዘብ አስተዳደር በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉትን ሥርዓቶችና መመዘኛዎች ተከትሎ መፈፀሙን ያረጋግጣል፣ በዋናው ኦዲተርም እንዲመረመር ያደርጋል።
18) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ያከናውናል።

22. <u>የማዕድን ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የማዕድን ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕግ ማዕቀፍ ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርት ፍለጋን በበላይነት ይመራል፤ ምርቱን ወደ ገበያ ለማሸጋገር የሚያስችል ዘመናዊ አሠራሮችን ይዘረጋል፤
3) የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋንና የሥነ-ምድር መረጃዎች ማደራጀት ሥራን ያስተባብራል፣ መረጃዎችን ለኢንቨስትመንትና ለልማት ተደራሽ ያደርጋል፤
4) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ኢንቨስትመንትና ልማት የግል ዘርፉ ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤
5) በማዕድን፣ በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ ባለሃብቶች እና ኩባንያዎች አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የዘርፉን ቁጥጥር ፈቃድ ይሰጣል፤ የክፍያ ግዴታቸውን መወጣታቸውን ይከታተላል፤ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤
6) ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ እና ከውጪ የሚገቡ ማዕድንና የማዕድን ውጤቶች የሆኑ የሲሚንቶ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ሴራሚክ፣ ማርብልና ግራናይት፣ የብረት ማዕድን፣ የተለያዩ የማዕድን ኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ የፖታሽና የማዳበሪያ እና የፔትሮሊየም ልማት ውጤቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ የምርመራና የምርት ፈቃድም ይሰጣል፣ ከፍለጋ እስከ ምርት ያለውን የምርት ሰንሰለት ውጤታማ እንዲሆን ሙሉ ድጋፍ ያደርጋል፤
7) ተጨማሪ እሴት ያላቸውን የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርቶች ላይ የሚሰማሩ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የኢንቨስትመንት እና ማምረት አቅም ለማጎልበት የምርምር፣ የክህሎት ልማት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን ያበረታታል፤ ይደግፋል፤
8) የማዕድን ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
9) ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በባሕላዊ መንገድ የሚመረቱ ማዕድናት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል ውጤታማና ቀልጣፋ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤
10) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በባሕላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ምርትና ግብይት ሕጋዊ መስመር እንዲይዝ አስፈላጊ ሥርዓትና መሠረተ-ልማቶችን ይዘረጋል፤
11) የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ሥራዎችን ለማፋጠን የሚውሉ የቤተ ሙከራና የማዕድን ጥራት ማረጋገጫ ማዕከላትን እንዲሁም የምርምርና የማሰልጠኛ ተቋማትን እንዳስፈላጊነቱ ያደራጃል፤
12) በማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት መስክ የሚፈለገውን የሰው ሀብት ለማልማት ከትምህርት ተቋማትና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
13) የማዕድንና ነዳጅ ሥራዎች በሚከናወንበት አካባቢ የአካባቢ ማህበረሰብን ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ የሕግማዕቀፍ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀደቁም በአግባቡ መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፣ በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን ይከታተላል፤

14) ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ፣ የከርሰ-ምድር ሀብት ዋጋን፣ የሮያሊቲ ክፍያንና የመንግሥትን የምርት ድርሻ ለመወሰን የሚያስችል ዋጋ ቀመር ይወስናል፤

15) በሌሎች ሕጎች ለማዕድን ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

23. <u>የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሥራ፣ የሥራ ስምሪትና ክህሎት እና ኢንተርፕረነርሺፕ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ከሀገሪቱ አጠቃላይ የልማት ፖሊሲና ከሥራ፣ ከሥራ ስምሪትና ክህሎት ዕድገት ጋር አብሮ ለማስኬድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

3) ከሚመለከታቸው የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፎች ጋር በመቀናጀት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የሥርዓተ-ሥልጠና ማዕቀፍ ይቀርፃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ በሚመለከተው አካል ለቴክኒክና ሙያ ተቋማት የወጡ ደረጃዎች መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

4) በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን የሙያ ትምህርት ጥራትና ተገቢነት የማረጋገጥ፣ የሙያ ደረጃና መስፈርት የማዘጋጀት እና በሁሉም የሙያ ዘርፎች በቂና ብቁ የሰው ኃይል አቅርቦት እንዲሟላ የማድረግ ሥራዎችን ይሰራል፤ ያረጋግጣል፤ ያስተባብራል፤

5) የሰው ኃይል ልማትን ለማፋጠንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ውጤታማነት ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ ይመራል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

6) በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት እና በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፎች መካከል ለሥራ ገበያና ስምሪት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስ በእርስ ትስስር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

7) በሥራ ገበያ ላይ የሚታዩ የክህሎት ክፍተቶችን በተመለከተ ወቅታዊ የዳሰሳ ጥናቶችን ያካሂዳል፤

8) የሥራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ በተለያዩ ዘርፎች የሚሰሩ ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤ የሥራ ዕድልን ለማስፋፋት በፌዴራልና በክልል መንግሥት አካላት፣ በግል ዘርፍ፣ መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ፣ በልማት አጋሮች እና ተቋማት መካከል ትብብር እንዲኖር ያግዛል፣ ያስተባብራል፤ ሥልጠናዎችና የሥራ ልምዶች ከሥራ ገበያ ፍላጎቶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ይሰራል፤

9) የኢንተርፕሬነርሺፕ ሥነ ምኅዳር ምቹ እንዲሆን እና የአንተርፕረነርሺፕ አቅም በሁሉም ሴክተሮች እንዲገነባና አንዲተገበር ድጋፍ በማድረግ ኢንተርፕረነሮች በኢኮኖሚው ውስጥ ለሥራ ፈጠራ፣ ሀብት እና እሴት ጭማሪ እና ሊዝነስና ለንግድ ምቹ ሥነ ምኅዳር ለመፍጠር በትብብር ይሰራል፤

10) ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ ዕድልና ስምሪት አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲስፋፉ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ለሥራ ፈላጊዎች ቅጥርና ምደባ በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ የቅጥር ዓይነት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር እንዲመቻች ያደርጋል፤

11) መደበኛ ያልሆነውን የሥራና የቢዝነስ ዘርፍ ወደ መደበኛ ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የቢዝነስ ልማት አገልግሎት ድጋፍ ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

12) አካል ጉዳተኞች የተለየ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ያመቻቻል፤

13) ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የተለየ ፓኬጅ ተቀርጾ ወደ ሥራ እንዲሰማሩ በማድረግ በጊዜ ገደብ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ያስተባብራል፤

14) ከስደት ተመላሽ ዜጎችን በዘላቂነት ለማቋቋም የሚያስችል የክህሎት ሥልጠናና የሥራ ዕድል ፈጠራ ፓኬጆች፣ ልዩ የብድር እና የቴክኒክ ድጋፍ ያመቻቻል፤

15) የጎብረት ሥራ ማኅበራት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

16) ለውጭ ሀገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያዊያንን የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ይቆጣጠራል፤

17) የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

18) ተቀማጭነታቸው ከአንድ ክልል በላይ የሆኑ ድርጅቶችን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

19) የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማኅበራትንና የሕብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፤ በእነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናውናል፤ በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በስምምነት ለመጨረስ የማስማማት አገልግሎት ይሰጣል፤

20) በሥራ ላይ የሚከሠቱ አደጋዎችና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የሙያ ጤንነትና ደኅንነት ደረጃዎች ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

21) የአሰሪና ሰራተኛን ሰላማዊ ግንኙነት ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

22) አሠሪዎችና ሠራተኞች በማኅበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤ በሀገር ዓቀፍደረጃ የሚደራጁትን የሠራተኛና የአሠሪ ማኅበራት ይመዘግባል፤

23) በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ፣ እንዲሁም የመንግሥት ወገንን ጨምሮ የሶስትዮሽ የውይይት መድረኮች እንዲደረጉ ድጋፍ ያደርጋል፤ የሥራ ክርክሮችን ከስተት ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ሲከሰቱም መፍትሄ የሚያገኙበትን የተቀላጠፈ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ያስፈጽማል፤

24) የአሠሪና ሠራተኛ ብሔራዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ሀገራዊ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ የሥራ ፈላጊዎችን መረጃ ይይዛል፤

25) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፡፡

24. <u>የሰላም ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የሰላም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ከሰላም ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሕጎችን ለማውጣት የሚስችሉ ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ሲጸድቁም በሥራ ላይ ያውላል፤

2) የሀገር ውስጥ ሰላምን ለማስጠበቅ አግባብ ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤ የሀገርና ሕዝብ ሰላም እንዲከበር የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤ በጎብረተሰቡ መካከል የሰላም፣ የመከባበርና የመቻቻል ባሕል እንዲዳብር የግንዛቤና የንቅናቄ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ያከናውናል፤ አተገባበሩን ይከታተላል፤

3) በተለያዩ ኃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች፣ እንዲሁም በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት፣ የባሕልና የኃይማኖት ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

4) በኃይማኖት፣ በብሔርና ሌሎች ምክንያቶች ሽፋን የሚደረግ የአክራሪነትና የጽንፈኛነትን አስተሳሰብ ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ያስፈጽማል፤

5) አለመግባባቶችን በምክክር የመፍታት ባሕል እንዲዳብር አግባብነት ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፤ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲወሰንም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

6) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሀገራዊ አንድነትና መግባባትን የሚያነለብት የባሕል ልውውጥ፣ የሥነ-ዜጋ ትምህርት የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

7) ለአካባቢያዊ ግጭቶች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ይለያል፤ ኅብረተሰቡ ወደ ግጭትና አለመረጋጋት እንዳያመራ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያመለክት ጥናት ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

8) የሀገር ውስጥ ሕገ-ወጥ መፈናቀልን ይከላከላል፤ የእርስ በእርስ ግጭቶች እንዳይከሰቱ እና በድንበር አካባቢ የሚኖሩ ዜጎች በጎረቤት ሀገራት ዜጎች ጉዳት እንዳይደርስባቸው በጥናት ላይ የተመሠረተ ቅድመ-ጥንቃቄ እና ዘላቂ መፍትሔ እንዲሰጥ ያመቻቻል፤

9) በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገርና በሕገ ወጥ መንገድ ሰውን ለሥራ ወደውጭ ሀገር መላክ ወንጀሎች ተከላካይ ብሔራዊ የትብብር ጥምረቱን ይመራል፤

10) በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር በማድረግ የፌዴራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር የግንኙነቱ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

11) በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 48 እና 62 (6) እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

12) አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ከክልሎች ጥያቄ ሲቀርብ በክልሎች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን መፍትሔ ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

13) ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያሉ የድንበር ማካለል ሥራዎች ከተከናወኑ በኋላ የድንበር አካባቢዎች ሰላማዊ ሆነው እንዲቀጥሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

14) በመንግስታት ግንኙነት ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1231/2013 መሠረት የተቋቋመውን የመንግሥታት ግንኙነት ሴክሬታሪያት ሥራዎች ይደግፋል፤ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

15) የፌዴራል መንግሥቱ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ሲወሰን አፈፃፀሙን ያስተባብራል፤

16) የሃይማኖት ድርጅቶችን ይመዘግባል፡፡

17) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል።

25. <u>የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያንና የሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) በፌዴራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና የሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጉዳዮችን እንዲያካትቱ ስልትና መስፈርቶች ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

3) ሴቶችና አካል ጉዳተኞች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ይነድፋል፣ ያስፈጽማል፤

4) ሴቶች በተለያዩ የመንግሥት አካላት በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤ በሀገር ዓቀፍደረጃ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

5) በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

6) ሴቶች በተለያዩ ዘርፎች የሚሰማሩባቸው የሥራ ዕድሎች መፈጠራቸውን፣ ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መቀረጻቸውን ያረጋግጣል፤ አተገባበሩንም ይከታተላል፤

7) የሴቶችና የሕፃናት መብቶችን በተመለከተ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎችን ይሰራል፣ ይመራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

8) በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችን ለመከላከል እንዲሁም ጥቃቶች ሲፈጸሙ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስትራቴጂ ይነድፋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያውላል፤

9) ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶችና ሕፃናት የተሟላ የጤና፣ የሥነ ልቦና፣ የሕግና የተሃድሶ አገልግሎት የሚያገኙባቸው ማዕከላት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ይሰጣል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

10) የሕፃናት መብትና ደኅንነት እንዲጠበቅ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ያስተባብራል፤

11) የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የሕፃናት መልካም አስተዳደግና ስብዕና ግንባታ፣ ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና ተሀድሶ ላይ ለወላጆችና አሳዳጊዎች ተገቢውን ግንዛቤና ሥልጠና በመሥጠት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፤

12) በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡና ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት ጉዲፈቻን ጨምሮ በሀገር ውስጥ ባሉ አማራጭ ድጋፍና እንክብካቤ ዘዴዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ በዓለም ዓቀፍ ጉዲፈቻ ከሀገር የወጡ ኢትዮጵያዊ ሕፃናት በእንክብካቤ እንደተያዙ ለማረጋገጥ ጉዳያቸውን ይከታተላል፤

13) ሕፃናት ከሀገሪቱ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የልማት ተቋማት ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ስልት ይቀይሳል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

14) ቤተሰብ እንደኅብረተሰብ ዋና መሠረት የተሰጠውን ሕገ-መንግሥታዊ ጥበቃ በተግባር ለማዋል የሚያስፈልጉ ስልቶችን ከሚመለከታቸው ክልላዊ መንግሥት አካላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይነድፋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

15) ሴቶች፣ ሕጻናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን የጤና፣ የትምህርት፣ የመረጃ፣ የቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት እና ለሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

16) የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ በተለይም ሕጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

17) የማኅበራዊ ጥበቃ እና ዋስትና ሥርዓትን በማስፋፋት ደረጃ በደረጃ ለዜጎች እንዲዳረስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

18) የማኅበራዊ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን መረጃ ዘመናዊ በሆነ መንገድ ለማሰብሰብ ለማደራጀትና ለመተንተን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

19) ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና የሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንደፍላጎቶቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

20) ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከቱ ዓለም ዓቀፍ ውሎችን በሕግ መሠረት ይዋዋላል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፤

21) የሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፤

22) በአዋጅ ቁጥር 676/2002 እና በአዋጅ ቁጥር 1178/2011 ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት ውጪ የሆኑ ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ ያውላል፡፡

23) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

26. <u>የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የባሕልን፣ የጥበብ ኢንደስትሪን የሚመለከቱና የቱሪዝም ልማትና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕግ ማዕቀፎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) በኢትዮጵያ የሚገኙ ልዩ ልዩ ባሕላዊ ዕሴቶች እና ሀገር በቀል ዕውቀቶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና እንዲለሙ ያደርጋል፤

3) የባሕል ዘርፉ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት አስተዋጽዖ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

4) የዕደ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብና የሥነ ጥበብ የፈጠራ ችሎታዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የሀገሪቱ የፊልምና ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበትን አግባብ ያመቻቻል፤

5) በባሕል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባሕል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

6) ማኅበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮች እንዲታረሙና እንዲስተካከሉ ይሰራል፤

7) በዘርፉ ውጤታማ የፈጠራ ሥራዎችን ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

8) የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዲጠኑ፣ እንዲለሙ፣ ሥነ-ጽሑፎቻቸው እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

9) የትርጉም አገልግሎትና የአስተርጓሚነት ሙያ ዕውቀት እንዲዳብርና እንዲስፋፉ የሚያደርጉ ሥራዎችን ያከናውናል፤ ደረጃውን የጠበቀ የሥራ ቋንቋ አጠቃቀም እና የትርጉም አገልግሎት እንዲኖር ይደግፋል፣ ክትትል ያደርጋል፤

10) የሀገሪቱን የቱሪዝምና የኢኮ-ቱሪዝም መስህቦች በአግባቡ እንዲለዩና እንዲታወቁ ያደርጋል፤ አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦች እንዲለሙ፣ ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲጎለብቱ እና የቱሪዝም ምርትና አገልግሎት በዓይነትና በመጠን እንዲያድጉ በማድረግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ የግል ባለሀብቶችም በልማቱ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

11) የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ-ልማት እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤ ተጨማሪ አዳዲስ መሠረተ-ልማቶች እንዲገነቡ ያደርጋል፤

12) የሀገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

13) በፌዴራል መንግሥት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በአግባቡ እንዲጠበቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲመሩ የማድረግ ሥራን ያስተባብራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ይቀርፃል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

14) የሀገሪቱን የቱሪስት መስህቦች በዓለም ዓቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎችን በማሟላት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

15) የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ገበያ ፍለጋና ማስተዋወቅ፣ የገበያ ትስስር እና ብራንዲንግ ሥራዎችን በማቀናጀትና በመምራት የሀገሪቱ ን የቱሪዝም ሃብቶች፣ መስህቦችና መልካም ገፅታ በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ በስፋት ያስተዋውቃል፤ አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን ይፈጥራል፤ የዘርፉን የገበያ ድርሻ እንዲያድግ ያደርጋል፤

16) ለቱሪዝም መስህብነት ለሚውሉ ምርትና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽና በየጊዜው በማሻሻል በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

17) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፤ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤

18) ሥልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ አገልግሎት ለሚሰጡ ወይም ሕግ በሚፈቅደው አግባብ በውጭ ባለሀብቶች ለሚካሄዱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

19) የቱሪዝም ዘርፍ መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓት ይዘረጋል፤ የቱሪዝም መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤ ከብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት በሀገራዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ውስጥ ለማዋሃድ ሥርዓት ይዘረጋል፤

20) ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር በመፍጠር ይሰራል፤ የመንግሥትና በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ የግል ዘርፍ አካላትን ያስተባብራል፤ ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል፤ ጥራት ያለው የቱሪዝም አገልግሎትና የቱሪስቶችን ደኅንነት ለማረጋገጥ ያሉትን ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች ለማስተባበር በቱሪዝም ዙሪያ የጋራ መድረክ ይፈጥራል፤

21) በሌሎች ሕጎች ለቱሪዝም ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን እና ባሕልን በሚመለከት ለባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

27. <u>የብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የልማት፣ የሀገራዊ የስታቲስቲክስ፣ የሥነ-ሕዝብ፣ ሀገራዊ የመሬት አጠቃቀም፣ የአየር ንብረት ለውጥንና አካባቢን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) ብሔራዊ ስትራቴጂ የፖሊሲዎች ፣ የልማት ፕላኖችና ፕሮግራሞች የሚመነጩበትና የሚጣጣሙበት የበላይ የአቅጣጫ ሰነድ ሆኖ እንዲያገለግል ያደርጋል፤ በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረዥም ዘመን የብሔራዊ ስትራቴጂ ትግበራን የሚመለከቱ የፖለሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያስተባብራል፤ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፤

3) ሀገራዊ የረጅም ጊዜ አመላካች የልማት ፕላን ያዘጋጃል፤ በዚህም ላይ ተመስርቶ የሀገሪቱን የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ፕላንና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

4) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የልማት ፕላን አካል የሆነውን ሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ትንበያና የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፉ የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንት እና የወጪና የገቢ ንግድ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤

5) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በመላ ሀገሪቱ የተመጣጠነ ልማት እና ዘለቄታዊ የመሬት አጠቃቀም ለማረጋገጥ የሚያስችል ሀገራዊ የመሬት አጠቃቀም ፕላን እና የስፓሻል ፕላን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ያስተባብራል፤

6) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሎችንና የዜጎችን ፍትሐዊ የመልማትና የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

7) የኢኮኖሚና የልማት ፖሊሲ ትንተናና ጥናቶች ያካሂዳል፤ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያስተባብራል፤ ስትራቴጂያዊ የማኅበራዊና ኢኮኖሚ ጉዳዮችን ይለያል፤ በትንተናና ጥናቶች በሚገኙ ውጤቶች መሠረት የፖሊሲ ምክረ-ሀሳቦችን ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል፤ በተለያዩ አካላት የሚመነጩ የልማት ፖሊሲዎችን የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

8) የልማት ፕላንን ለማሳካት እንዲሁም የመንግሥት የማስፈፀም አቅም ለማጠናከርና ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር የአስፈጻሚ ተቋማት ሪፎርም እና የሥርዓት ማሻሻያ ጥናት ያካሂዳል፤ በጥናቱ ላይ ተመስርቶ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የሥልጣንና ተግባራት ወሰን፣ አወቃቀርና አደረጃጀትን በተመለከተ የውሳኔ ሀሳብ ለመንግሥት ያቀርባል፤

9) የሀገሪቱን የልማት ፕላን ለማስፈፀም የሚያግዙ የልማት ፕሮጀክቶችን በመለየትና በመቅረጽ በሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ተጨማሪ ዝግጅቶች ተደርጎባቸው ተግባራዊ እንዲደረጉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

10) በመንግሥት በጀት፣ በመንግሥት ዋስትና ብድር እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ የበጀት ምንጮች እንዲከናወኑ የታቀዱ የፌዴራል መንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአዋጭነትና አስፈላጊነት ግምገማ ያካሂዳል፤ አዋጭነታቸው የተረጋገጡ ፕሮጀክቶችን ቅድሚያ ለመስጠትና ለመምረጥ የሚያስችል መስፈርት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት ያዘጋጃል፤ የልማት ፕሮጀክቶችን ቅደም-ተከተል ያስይዛል፤ ሀገራዊ ፋይዳቸው ከፍተኛ የሆኑ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ እንዲሰጣቸውና ተገቢው የፋይናንስ ሀብት እንዲመደብላቸው ያደርጋል፤ የልማት ፕሮጀክቶችን የሱፐርቪዥን ሥራ ይመራል፤ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

11) ሕገ መንግሥታዊ የሥልጣን ክፍፍሉን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የልማት ፕላኖቻቸውን ከብሔራ ስትራቴጂ ጋር እንዲያጣጥሙ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ የፌዴራል–ክልል የፕላን፣ የክትትልና የግምገማ ቅንጅት ሥርዓት ይዘረጋል፤

12) ብሔራዊ ስትራቴጂ በመንግሥት ተቋማት፣ በክልሎችና በዜጎች ዘንድ እንዲታወቅና ባለቤትነት እንዲኖረው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል፤

13) የልማት ፕላን፣ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት እንዲሁም የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት እና አጋዥ መሠረተ-ልማት ይዘረጋል፤ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የቴክኒካል ምክር አገልግሎትና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

14) ሀገራዊ የልማት ፕላን፣ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በየጊዜው ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ የሀገራዊ የልማት ሥራዎች አፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀት ለመንግሥት ያቀርባል፤

15) የብሔራዊ የኢኮኖሚ አካውንትና ስታቲስቲክስ በማዘጋጀት ዓመታዊና የሩብ ዓመት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ግምት ያካሂዳል፤ የተጣጣመ እና ደረጃውን የጠበቀ ክልላዊ የኢኮኖሚ አካውንት መዘርጋቱን ይከታተላል፤ ክልሎች የራሳቸውን የኢኮኖሚ አካውንት እንዲያዘጋጁ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

16) ኦፊሴላዊ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና ሥነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ የመረጃ ጥራት ክትትል ያደርጋል፤ ይገመግማል፣ እውቅና ይሰጣል፤

17) የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥን የሚመለከቱ ሥራዎችን ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

18) በሌሎች ሕጎች ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል።

28. <u>የትምህርት ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎችና እና ፕሮግራሞች ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ የትምህርትና የትምህርት ተቋማትን ስታንዳርድ ያወጣል፣ ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤ በተቋማቱ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርት መሰጠቱን ይከታተላል፤

3) የአጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲና ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት ያደረጉ ሀገር ዓቀፍ ፈተናዎች ዝግጅት፣ ሪከርድ መያዝና የምስክር ወረቀት የመስጠት ሂደቶችን በበላይነት ያስተባብራል፤

4) ትምህርትን በተመለከተ ሀገራዊ የአህዝቦት ተግባራትን ያከናውናል፤

5) ጥራቱን የጠበቀ የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፤

6) የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አፈጻጸም ይከታተላል፤

7) በመንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር ሥርዓት መሠረት የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የካፒታል ፕሮጀክቶችን ለአዋጭነት ግምገማ፣ ቅድመ ተከተል የማስያዝና መረጣ ለብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር ያቀርባል፤

8) የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ምደባ አፈጻጸም ፍትሐዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

9) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በጥናትና ምርምር የጎለበቱ እንዲሆኑ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፣ ይተገብራል፤ የጥናትና ምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ያመቻቻል፤

10) ከኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስ በርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

11) በዚህ አዋጅ የተቋቋመውን የብሔራዊ የምርምር ፈንድ እና ምክር ቤት በምክትል ሰብሳቢነት ይመራል፤

12) በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፱52/20፲፩ ለከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ሥራ ላይ ያውላል።

13) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል።

29. <u>የሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የሎጅስቲክስ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሎጂስቲክስ ዘርፍ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ያመነጫል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) የልማት ማዕከላትንና የዕድገት ኮሪደሮችን የሎጂስቲክስ ፍላጐት ለማሟላት የየብስ፣ የአየርና የባህር ትራንስፖርት አገልግሎቶች የተቀናጁ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

3) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሁለንተናዊ ሀገራዊ የሎጂስቲክስ ውህደት መናበብ እንዲፈጠር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ለአፈፃፀሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

4) የሀገሪቱን የሎጅስቲክስ እና ትራንስፖርት መሠረተ-ልማቶች ማስተር ፕላን፣ ዕቅድና መርሀ-ግብሮች ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፤ የሀገሪቱን የልማትና ዕድገት ኮሪደሮች ሎጂስቲክስ ፍላጎት ለማሟላት የየብስ፣ የባህር፣ የአቪዬሽንና ሌሎች የሎጂስቲክስ መሠረተ-ልማት ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በሚመለከታቸው አካላት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

5) በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ሕጎች ለከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ከተሰጠ ሥልጣን ውጪ የሎጅስቲክስ መሠረተ-ልማቶች መዘርጋታቸውን፣ መስፋፋታቸውንና መጠገናቸውን ያረጋግጣል፤ አስተማማኝና ደህንነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆኑ የአጠቃቀም፣ የአያያዝ፣ የአስተዳደርና የቁጥጥር ደረጃዎችንና ሥርዓቶችን ይወስናል፤ ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣል፤

6) የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ የደኅንነት ደረጃዎችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

7) የትራንስፖርት ማኔጅመንት ሥርዓቱን ለማሻሻልና የመንገድ ትራፊክ ደኅንነት ችግርን በመሰረታዊነት ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናውናል፤ ይተገብራል፤

8) የሀገሪቱ የሎጂስቲክስ ሥርዓት የወጪና ገቢ ንግድ ሥራዎችን ቀልጣፋና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ እንዲዘረጋ ያደርጋል፤

9) ለሀገሪቱ ጠቀሜታ ያላቸውን የወደብ አገልግሎቶች ያጠናል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ከወደብ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ከሌሎች ሀገራት ጋር የስምምነት ሰነዶችን ይፈራረማል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

10) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሎጅስቲክስ ዘርፍ ላይ በቀጣናዊ እና ዓለም ዓቀፍ ደረጃ ትብብር እንዲጎለብት ያደርጋል፤ በዘርፉ የትብብር ሥራዎችን ይመራል፤ የትብብር ስምምነት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

11) የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር በሁለቱ አገሮች መካከል የተደረገውን ስምምነት ይከታተላል፤

12) በሎጅስቲክስ ዘርፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ እንዲስፋፉና እንዲዳብሩ ያደርጋል፤

13) የሎጅስቲክስ መሠረተ-ልማቶችና አገልግሎቶች በአካባቢና አየር ንብረት የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን በመለየት ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

14) በሌሎች ሕጎች ለትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

30. <u>የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድን የሚመለከቱ ቀጣናዊ በተለይም ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖር የንግድና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ፣ ሀገራዊ የጥራት መሠረተ ልማቶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና እንዲዘምን፣ ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፤ በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

3) ከነዳጅ እና የነዳጅ ውጤቶች ውጭ የሆኑ የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን እንደአስፈላጊነቱ ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

4) አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ቀላል፣ ወጪ ቆጣቢና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አገልግሎቱን ይሰጣል፤ የተሰጡ የንግድ ፈቃዶች ለተሰጠባቸው ዓላማ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

5) የንግድና የዘርፍ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

6) የሀገሪቱ የወጪ ንግድ የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ስትራቴጂያዊ ትኩረት በሚሰጣቸው ዘርፎች ምርቶች ለውጭ ገበያ በማቅረብ ረገድ የታቀደውን ዕድገት ለማምጣት የሚያስፈልጉ ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፤ ይተገብራል፤ ያስፈጽማል፤ ይደግፋል፤

7) የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

8) አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ንግድ ግንኙነቶችን ይመሠርታል፤ ያስፈጽማል፤

9) የወጪና የገቢ ንግድ፣ በምርት፣ በሀገር ውስጥ ገበያ አንዲሁም በአጠቃቀም ወቅት በተለያዩ ተቋማት የሚደረጉ የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች የተቀናጁ እንዲሆኑ እና ድግግሞሽን የሚያስቀሩ እና ከዓለም ዓቀፍ ስታንድርድ አንፃር የተናበቡ እና የንግድና የቢዝነስ አሠራርን የሚደግፉ እንዲሆኑ የሚመለከታቸውን ተቋማት ያስተባብራል፤

10) አግባብነት ባለው ሕግ ለሌላ ተቋም የተሰጠ ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት በተዘረጉ የጥራት ማስጠበቂያ ሥርዓቶች መሠረት ይቆጣጠራል፣ ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ይቆጣጠራል፤

11) የወጪና ገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፤

12) አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ለሌላ አካል የተሰጠ ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣ በሌሎች አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

13) የሀገሪቱ ን ሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል፤

14) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 (እንደተሻሻለ) ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን የተሰጡ ከዳኝነት ችሎት ሥራ ውጪ የሆኑ ተግባርና ኃላፊነቶችን በሥራ ላይ ያውላል፡፡

15) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

31. <u>የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) በኢንዱስትሪ በተለይም ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት ትኩረት የሚሰጣቸውን ዘርፎችና ንዑስ ዘርፎች ካላቸው አንጻራዊ ጠቀሜታና እምቅ አቅም አኳያ ይለያል፤ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርኃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

3) ለዘርፉ እድገት ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ ስለሚመጣበት ሁኔታ ስልቶችን ይነድፋል፤ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

4) የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስትመንት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ በሥሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በዋናነት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግ ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ያስፈጽማል፤

5) ለማዕድን ሚኒስቴር ከተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ የኢንዱስትሪ ገቢ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲተኩ ድጋፍ ያደርጋል፤

6) በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤

7) የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ውጤታማ እንዲሆኑ የማትጊያ ስልት ይቀይሳል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

8) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤

9) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤ የምርጥ ተሞክሮ ቀመራና አጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤

10) በዘርፉ ምርምርና ጥናት ለሚያካሂዱ አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የኢንዱስትሪዎችን እና የማኑፋክቸሪንግ አቅምና ተወዳዳሪነትን እንዲያድግ ያደርጋል፤

11) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም ዓቀፍተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

12) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለኢንዱስትሪ በተለይም ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አስፈላጊ የሆነው የሰው ኃይል ፍላጎት እና አስተማማኝ ግብዓት ለማሟላት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

13) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፤

14) የኢንዱስትሪ የዘርፍ ማኅበራት እና የሙያ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፤ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

15) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

32. <u>የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የኢኖቬሽን አጠቃቀም ባሕል እንዲጎለብት የሚያስችል ፖሊሲ ያመነጫል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀደቅም ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤ የሀገሪቱ ሥርዓተ-ትምህርት እና ሥርዓተ-ሥልጠና ከሳይንስ ልማት፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት አንፃር መቃኘቱን ያረጋግጣል፤

2) የሀገራዊ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፤ ለሀገሪቱ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የጥናትና ምርምር መስኮችን ይለያል፤ ሀገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤

3) ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች ዕድገት አስተዋጽዖ ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

4) አዳዲስ የኢኖቬሽን ሃሳቦችን ያበረታታል፤ ወደ እሴት ተለውጠው ለሀገራዊ ብልጽግና የሚያደርጉት አስተዋፅዖ ውጤታማ እንዲሆን ይከታተላል፤

5) በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም ግንባታን ይደግፋል፤ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መዳበር የበለጠ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ግለሰቦችን፣ የሙያ ማኅበራትንና የጥናትና ምርምር ተቋማትን ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

6) የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለመዳሰስ፣ ተገቢ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግና በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

7) ሀገር-በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለማሻሻል፣ ለማሳደግና ለገበያ ለማቅረብ የሚደረጉ ጥናቶችን፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎችን ያበረታታል፤ ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ በሙከራ ሞዴል ለባለድርሻ አካላትና ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፤

8) በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ ይመዘግባል፤ የማጠቃለልና ጥበቃ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያስተባብራል፤ ለቀጣይ ሥራ እንዲውሉ ያደርጋል፤

9) በትምህርት ቤቶች፣ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ወይም በግል ፈጣሪዎች የሚሰሩ ሳይንሳዊ ግኝቶች ፋይናንስ አግኝተው ወደ ናሙና እና ምርት እንዲሸጋገሩ የሚያስችል የድጋፍ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፤

10) በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ያሉ አገልግሎቶች በውጤታማነት ጥቅም ላይ አንዲውሉ የላብራቶሪ አገልግሎቶችን ያቀናጃል፤ ከፍተኛ ፋይናንስ የሚፈልጉ እና በሀገር ደረጃ በማዕከል መቀናጀት እና መደራጀት ያለባቸውን ላብራቶሪዎች በጥናት ላይ በመመሠረት በመለየት የሚመለከታቸውን አካላት ባሳተፈ መልኩ በመንግት ሲፈቀድ አንዲደራጁ ያደርጋል፤

11) ለተመረጡ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምር የሚውሉ ዓለም ዓቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤተ-ሙከራና የሰርቶ ማሳያ ማዕከላትንና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፓርኮችን በማቋቋም የሀገር ውስጥ የፈጠራ ክህሎት እንዲያድግ ድጋፍ ያደርጋል፤

12) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ጥራታቸው፣ ደኅንነታቸውና አስተማማኝነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውንም ይቆጣጠራል፤

13) የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ በተለይ የዲጂታል መሠረተ-ልማቶች ለማስፋፋት የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል፤

14) የመንግሥት አገልግሎት በቴክኖሎጂ የተደገፈና ቀልጣፋ እንዲሆን ይሰራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤ ለኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የፖሊሲ ድጋፍ ያደርጋል፤

15) የጨረራና ጨረር አመንጪ ቁሶች አጠቃቀምና አወጋገድ ቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

16) ለክልሎች ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ተቋማት አቅም ግንባታ አስፈላጊውን የሙያና ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ በክልሎች መከናወን ያለባቸውን የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ተግባራትን በመለየት የጋራ መግባባት ተደርሶባቸው በየደረጃው ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል።

17) በዚህ አዋጅ የተቋቋመው የብሔራዊ የምርምር ፈንድ እና ምክር ቤት በሰብሳቢነት ያስተባብራል፤ የምክር ቤቱ ሴክረታሪያት ሆኖ ያገለግላል።

18) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

33. <u>የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የከተማና ኮንስትራክሽንና መሠረተ ልማትን ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ እና መሠረተ ልማት በውጤታማነትና በቅንጅት መከናወኑን የሚያረጋግጡ፣ የከተማ መሬትን እና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመመዝገብ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሀገራዊ የተቀናጀ የመሠረተ-ልማት፣ መዋቅራዊ እና ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

3) የመንገድ እና አጠቃላይ ኮንስትራክሽን መሠረተ-ልማት ውጤታማነትን ያረጋግጣል፣ በመንገድና ኮንስትራክሽን መሠረተ-ልማቶች ላይ የሚፈፀሙ አስተዳደራዊ ጥሰቶችና የሚወሰዱ እርምጃዎች በሕግ እንዲወሰን ያደርጋል፡፡

4) በመንገድ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 66/1989 ለተቋቋመው ቦርድ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤ በአዋጁ ለመንገድ ፈንድ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ ያውላል፤ ፈንዱ ለተቋቋመለት ዓላማ እንዲውል ያደርጋል፤

5) በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የከተሞች መዋቅራዊና መሠረታዊ ማስተር ፕላን ዝግጅትን ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6) አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የተቀናጀ የአከታተም ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ከተሞች ከሀገር ዓቀፍና ከክልል ዓቀፍ የልማት ዕቅዶችና ከተቀናጀ የከተሞች ማስተር ፕላን ጋር ተጣጥመው የሚመሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

7) ከገጠር ወደ ከተማ የሚሸጋገሩ አካባቢዎችን በተመለከተ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን፣ የልማት ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ስታንዳርዶችን ያወጣል፣ ይቆጣጠራል፤

8) ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናቶችን ያደርጋል፣ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ያመነጫል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤ ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

9) የተመጣጠነ የከተሞች ዕድገትና የሕዝብ አሰፋፈር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመቀናጀት ይተገብራል፤

10) የከተሞችን ፈርጅ እና ሚና መወሰኛ መመዘኛ ያወጣል፤ የከተሞችን ፅዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፤ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

11) የከተማ ፕላን እና ኦብዘርቫቶሪ ሥራዎችን ያከናውናል፤ አግባብነት ካላቸው የከፍተኛ ትምህርት እና የምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

12) የከተሞችን መሬት በቁጠባ እና በውጤታማነት መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ የአሰራር ስልት ይነድፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

13) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ የከተማ መሬት ይዞታ እና የንብረት ካሳ ቀመርና የነጠላ ዋጋ ያዘጋጃል፤

14) የነፃ ገበያ ሥርዓት ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የካዳስተር እና ከመሬት ውጪ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይት ሥርዓት እንዲገነባ ያደርጋል፤ በከተሞች ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የለማ መሬት አቅርቦት ለማረጋገጥ ድጋፍ ይሰጣል፤

15) የከተማ መሬትና ከመሬት ጋር የተያያዘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ መለያ ኮዶች ሥርዓት ያወጣል እንዲሁም የመለያ ኮዶቹ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ በከተሞች ተጣጥመው ተፈፃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

16) የከተማ መሬትና ከመሬት ጋር የተያያዘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባን የሚያከናውኑ ተቋማት እንዲያደራጁ ለክልል ከተሞች ድጋፍ ያደርጋል፣ ተቋማቱ ደረጃውን የጠበቀ ምዝገባ ማከናወን እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤

17) የካዳስተር ባለሙያዎች ሥልጠና ፕሮግራም ስለሚስፋፋበትና የሙያ ብቃት የሚረጋገጥበት ሥርዓት ስለሚጠናከርበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

18) ለዜጎች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ለማሟላት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ በሚመለከታቸው አካላት ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይደግፋል፤ በቤቶች ልማት ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

19) ሀገር ዓቀፍ የሪል ስቴት ልማትና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ የሪል ስቴት ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ሲፀደቅም ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

20) ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ እና መልካም አስተዳደር እንዲያሰፍኑ የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፣ የመሠረተ-ልማት አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፤

21) የከተሞች ልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሥርዓት ያጠናል፣ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ለአፈፃፀሙም ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

22) የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮችን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን እና መሠረተ-ልማት ሥራ እንቅስቃሴዎችን ይደግፋል፣ይከታተላል፤

23) በከተሞች ምግብ ዋስትና ማዕቀፍ የሚከናወኑ ከግብርና ሥራዎች ውጪ የሆኑ በከተማ ፕላን እና አገልግሎት አሰጣጥ ወሰን ውስጥ ያሉ ሥራዎችን ያስተባብራል፤

24) በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤ ሀገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ በዲዛይን፣ በጨረታና፣ በኮንትራት ይዘት ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

25) በማንኛውም ዘርፍ የሚደረጉ የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ግዢዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር መደረጉን ይከታተላል፤ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ደረጃ መውጣቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፤

26) በፌዴራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ የሕንፃ ኮድና ስታንዳርዶች በከተሞች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ሃይል አቅም እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፤

27) በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ያካሂዳል፤ የሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ግብዓት መጠቀምን ያበረታታል፡፡

28) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

34. <u>የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ወጣቶችና ስፖርትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) በፌዴራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልትና መስፈርቶች ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

3) ወጣቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

4) ወጣቶች እንደፍላጎቶቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ አቅማቸውንም ይገነባል፤

5) ወጣቶች በተለያዩ ዘርፎች የሚሰማሩባቸውን የሥራ ዕድሎች እና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የተቀረጹ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ያረጋግጣል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል፤ ይደግፋል፣ በቅንጅት ይሰራል፤

6) የወጣቶች መብትና ጥቅሞችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

7) የበጎ ፈቃደኝነት ሥራዎችን ይደግፋል፤ በበላይነት ያስተባብራል፤

8) ሕዝቡን በስፖርት ለሁሉም እና ባሕላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤

9) የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንና የስፖርት ማበልጸጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፤

10) የስፖርት ፋሲሊቲዎች የሚተዳደሩበትን ስልት ይቀይሳል፤

11) የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

12) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ሕክምና አገልግሎት ያደራጃል፣ በስፖርት አበረታች መድኃኒቶችና እፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

13) የስፖርት ማኅበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፣ በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማኅበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ የስፖርት ማኅበራት ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ የሚውል ገቢ ማመንጨት እንዲችሉ ከአላማቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሥራዎች እንዲያከናውኑ ይፈቅዳል፤

14) ሀገር ዓቀፍና ዓለም ዓቀፍ የስፖርት ውድድሮች ሲዘጋጁና ሲካሄዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ብሔራዊ ስፖርት ልማት ፈንድ በሕግ የሚቋቋምበትን ስልት ይቀይሳል፤

15) የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ድጋፍ ይሰጣል፣ ከውጪ የሚገቡበትንም ሁኔታ ያመቻቻል፤

16) በሌሎች ሕጎች ወጣቶችን በሚመለከት ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ስፖርትን በሚመለከት ለባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

35. <u>የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ውሃና ኤነርጂን ጂአተርማል ጨምሮ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2) የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሶች ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ የፖሊሲ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችንና ምርምሮችን ያደርጋል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ይተገብራል፤ ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀምን ለማስፈን የሚያግዝ ዘላቂ እና የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፤
3) በተፋሰሶች ውስጥ የሚተገበሩ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶችና እንቅስቃሴዎች ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ የተፋሰሶችን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ እቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፣ ይጠቀማል፤ ተፋሰሶችን ከብክለትና ከጉዳት ለማዳን ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች በጥናት ይለያል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይተገብራል፤ የውሃ አካላትንና ተያያዥነት ያላቸውን ሥነ-ምህዳሮች ይንከባከባል፤ ያስተዳድራል፤
4) የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የሀገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት በመጠንና በጥራት ይለያል፤ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ የውሃ ሀብት ልማትና አስተዳደር እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮችን ይቀርፃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
5) ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይወስናል፤
6) ሀገራዊ ወሰን ተሻጋሪ የውሃ አካላት አጠቃቀም ላይ ጥናት ያካሂዳል፤ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ዓለም ዓቀፍ ውሎችን ይደራደራል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) በተጠቀሱት የውሃ አካላት ላይ የውሃ ሥራዎች ለመሥራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፈቃድ ይሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤
8) ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል፤ የውሃ ብክለት እንዳይኖር ይቆጣጠራል፣ ክትትል ያደርጋል፤
9) የጎርፍ መከላከያ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ትንበያ ሥራን ያከናውናል፣ ከጎርፍ እና ከድርቅ ጋር በተያያዘ የተፈጥሮ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የሰዎችና የእንስሳት ህይወት እና ንብረት ከአደጋ ለመታደግ አግባብነት ካላቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎችን ያከናውናል፤
10) የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት እንዲስፋፋ ድጋፍ ያደርጋል፣ የጎርፍ ስጋት ቅድመ-ትንበያ አቅምን ለማሳደግ በዘርፉ ሚና ያላቸውን አካላት ይደግፋል፤ በቅንጅት ይሠራል፤
11) የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ በመጠጥ ውሃ አቅርቦትና የሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

12) ሀገራዊ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን የጥናትና ዲዛይን፣ የግንባታና የተቋማት አስተዳደር መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶችና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

13) ከፌዴራል መንግሥት በጀትና ከውጪ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ግንባታዎች በጥናትና ዲዛይናቸው መሠረት የጥራት ደረጃውን ጠብቀው መከናወናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

14) በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ በአገልግሎት ሰጪነት፣ በአማካሪነት፣ በሥራ ተቋራጭነት፣ በምርትና ዕቃ አቅርቦት የተሰማሩ የግል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን አቅም ለመገንባት የሚያስችል ድጋፍ የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

15) የተለየ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የተቀናጀ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ የአስቸኳይ ጊዜ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ ይሰጣል፤

16) በውሃ ልማት ዘርፍ በመንግሥትና በግል አጋርነት የሚከናወኑ የውሃ ልማት ዘርፎችን ይለያል፤ የቁጥጥር ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ በሥራ ላይ ያውላል፤ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

17) ለክልሎች በውሃ ልማት ተቋማት አቅም ግንባታ አስፈላጊውን የሙያና ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ ሀገራዊ የውሃ ልማት ፖሊሲዎች፤ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞችን በየደረጃው ተፈፃሚ ለማድረግ በክልሎች መከናወን ያለባቸው የውሃ ልማት ተግባራትን በመለየት የጋራ መግባባት ተደርሶባቸው በየደረጃው ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

18) በአዋጅ ቁጥር 268/1994 ለተቋቋመው ቦርድ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤ በአዋጁ ለውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ ያውላል፤ ፈንዱ ለተቋቋመለት ዓላማ እንዲውል ያደርጋል፤

19) የአገሪቱን አጠቃላይ የኢነርጂ ፍላጎት፣ አቅርቦትና ሀብት አቅም መሠረት ያደረገ የተቀናጀ የኢነርጂ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በየጊዜው ያሻሽላል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤ የኢነርጂ ልማትና አቅርቦት ከአገሪቱ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር ይሠራል፤ የኢነርጂ የክልላዊ ትስስርና የንግድ ትብብርን ያበረታታል፤

20) የውሃ፣ የፀሐይ፣ የንፋስ፣ የጂኦተርማል፣ የባዮማስና ሌሎች ታዳሽ የኢነርጂ ምንጮችን ጨምሮ የአገሪቱን የኢነርጂ ሀብቶች ለማልማትና በዘላቂነት ለመጠቀም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ የኢነርጂ ቆጣቢነትን፣ ንጹህ የኢነርጂ አጠቃቀምንና የኢነርጂ ሽግግርን ያበረታታል፤

21) የኤሌክትሪክ ማመንጫ፣ ማስተላለፊያ፣ ማከፋፈያና የኢነርጂ አቅርቦት ልማትን ያቀናጃል፣ ይከታተላል፤

22) የኢነርጂ ዘርፍ የልማት ፕሮጀክቶችን ይለያል፣ ያቀናጃል፣ ያስተባብራል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤ የኢነርጂ ልማት ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጋቸውን የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የአቅም ማሳደግ ድጋፍ ለማግኘት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል፤

23) የግሉ ዘርፍ፣ የልማት አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በኢነርጂ ልማት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ የኢነርጂ ቴክኖሎጂ፣ ምርምርና ፈጠራ ልማትን ያበረታታል፣ ያስተባብራል፤ የአገር ውስጥ የቴክኖሎጂና የሰው ኃይል አቅም እንዲጎለብት ያደርጋል፤ የኢነርጂ ልማትና አቅርቦት በአገር ውስጥና በክልላዊ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል፤

24) የኢነርጂ አገልግሎት ተደራሽነትን በተለይም በገጠርና በኢነርጂ አቅርቦት ውስንነት ባለባቸው አካባቢዎች ለማስፋፋት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤ የገጠር የኢነርጂ ልማት ሥራዎች የማስተባበር፣ የማበረታታት እና የመደገፍ ሥራ ይሰራል፤ በኢነርጂ ዘርፍ የሚሠሩ የፌደራል መንግሥት ተቋማትን ሥራ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤

25) የኢነርጂ አቅርቦት ደኅንነት፣ ቀጣይነትና ተደራሽነት ላይ የሚያሰጋ ሁኔታ ሲከሰት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ተገቢውን የመከላከያና የምላሽ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

26) የውሃና ኢነርጂ ልማትና አጠቃቀም የሀብት፣ የመረጃ፣ የጥናትና የምርምር ሥርዓት ይዘረጋል፣ መረጃ ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

27) በጂኦተርማል ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች እና ኩባንያዎች አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፤ የክፍያ ግዴታቸውን መወጣታቸውን ይከታተላል፤ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤

28) የነዳጅ እና የነዳጅ ውጤቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል።

29) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

36. <u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሠረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2) ሀገሪቱ ባላት የውጭ ግንኙነት ጥቅሟና መብቷ እንዲጠበቅና በሌሎች መንግሥታት እንዲከበር ያደርጋል፤ ሀገሪቱ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፤
3) ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀዱ ዓለም ዓቀፍ ውሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ እንዲሁም ዓለም ዓቀፍ ውሎች እንዲፀድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤
4) ዓለም ዓቀፍ ባህሪ ያላቸው ግዙፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በሀገር ውስጥ ቢሰማሩ የተለየ ሕዝባዊ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ ሲታምን ከመንግሥት ጋር ስምምነት የሚፈጽሙበትን አሠራር ይዘረጋል፤
5) ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማቸው ዓለም ዓቀፍ ውሎች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
6) ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን ዓለም ዓቀፍ ውሎች በሙሉ የተመለከረላቸውን ዋናዎቹን ቅጂዎች መዝግቦ ይጠብቃል፤
7) የኢትዮጵያ መንግሥት በብዙ መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ዓለም ዓቀፍ ውሎችን አስቀማጭ በሚሆንበት ጊዜ ይኸው ባለአደራነት የሚጠይቀውን ተግባር ያከናውናል፤
8) ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ ሀገር መንግሥታትና ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ሁሉንም ግንኙነቶች ያስተባብራል፤
9) በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ ሀገራት መንግሥታት እንደራሴዎች፣ ቆንስሎችና የዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
10) በዓለም ዓቀፍ ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም ዓቀፍ ውሎች ለውጭ ሀገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፤

11) በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚሲዮኖችን እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኞች ጽሕፈት ቤቶችን ተግባራት ያስተባብራል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል፤

12) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች እና የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ መግቢያ ቪዛዎች ይሰጣል፤

13) በፕሮቶኮል ጉዳዮች ላይ መረጃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

14) የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በማካሄድ የሀገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣ የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመለየትና ለመሳብ፣ ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት፣ የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድዖ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ድጋፍ ይሰጣል፤

15) በፐብሊክ ዲፕሎማሲና ኮሙኒኬሽን ተግባራት የሀገር ገጽታን የመገንባትና ደጋፊዎችን የማበራከት ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

16) በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ በኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብና በኢትዮጵያ ወዳጆች የተመሠረቱ ማኅበራትን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

17) የዳያስፖራ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤

18) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የኢትዮጵያን ዓለም ዓቀፍ የድንበር ማካለል ሥራዎችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ምክረ-ሃሳቦችን የሚያቀርብ የቴክኒክ ቡድን ያደራጃል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤

19) ለፖሊሲ ውሳኔ ጠቃሚ እና አስፈላጊ የሆኑ የውጭ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፤ ለዚሁ ዓላማ የሚሆን የጥናት እና የመረጃ ማዕከል ያደራጃል፤ የጥናት እና ትንታኔ ውጤቱን ለሚመለከታቸው ተቋማት ያሰራጫል፤

20) አጠቃላይ ተልዕኮውን በአግባቡ ለመወጣት፣ ከደኅንነት እና ከሥነ ምግባር አኳያ የሚያጋጥሙ ክፍተቶችን ለማረም አስፈላጊ የሆኑ የሰው ኃይል እና የፋይናንስ አሠራር ሥርዓቶችን በመመሪያ እየወሰነ ይተገብራል፤

21) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል።

37. <u>የገቢዎች ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የገቢዎች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢ አፈፃፀም ለማሻሻል እና ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ለማድረግ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፤ በታክስ ሕግ መሠረት መመሪያ ያወጣል፤

2) ዘመናዊ የሀገር ውስጥ ገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

3) የፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢ የመሰብሰብ አቅም ግንባታን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ አሠራሮችን ይቀርፃል፣ ይተገብራል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

4) ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የሚያግዝ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

5) ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ይተነትናል፤ ጥቅም ላይ ያውላል፤

6) የታክስ ሕጎችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ግለሰብ ወይም ድርጅት እጅ የሚገኙ ሠነዶችን ይመረምራል፤ ይይዛል፤

7) ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስ እፎይታ መብቶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

8) ለክልል እና ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ ለሆኑ የከተማ አስተዳደሮች የገቢ ሰብሳቢ አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የፌዴራል፣ የክልል እና ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ ለሆኑ የከተማ አስተዳደሮች ታክስ አስተዳደር ሥርዓት የሚጣጣሙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤

9) ለሎተሪ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፤ የሎተሪ ጨዋታ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ የመሳሪያ ዓይነቶችና መመዘኛዎችን ይወስናል፣ ወደ ሀገር የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤ ሕገ-ወጥ የሎተሪ ሥራዎችን ይቆጣጠራል፤

10) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

38. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ለፊስካል በተለይም ለታክስና ለቀረጥ ሕጎች መሠረት የሚሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፣ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡

2) የፌዴራል መንግሥትን በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያ ይፈጽማል፤ የበጀቱን አፈፃፀም ይገመግማል፤

3) ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፌዴራል መንግሥትን የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ አዲት ሥርዓት ይዘረጋል፤ የአፈፃፀሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤ የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድር የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ አዲት ሥርዓቶች አንድ ወጥና የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

4) የፌዴራል መንግሥቱን የግዢና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋቱንና በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

5) የፌዴራል መንግሥት ንብረት የተጠቃለለ መዝገብ ይይዛል፤ የንብረት ምደባ፣ መለያ፣ ግምገማ፣ የዋጋ ቅናሽና የመመዝገቢያ ደረጃ ዓለም ዓቀፍ የመንግሥት ሒሳብ አያያዝ ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ ያወጣል፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የያዙትን ንብረት በሚያወጣው የአሠራር ሥርዓት መሠረት እንዲመዘግቡና በየጊዜው ሪፖርት እንዲያደርጉ ያደርጋል፤ የፌዴራል መንግሥት የተጣራ ሀብት መግለጫ አዘጋጅቶ ከመንግሥት ዓመታዊ ሒሳብ ጋር ያቀርባል፤

6) የፌዴራል መንግሥት አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል፤ በሕግ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ፈንዶችን ያስተዳድራል፤ በሌሎች ዘርፎች የሚተዳደሩ ፈንዶች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

7) ከመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ ከመንግሥት ዋስትና፣ ከንዑስ ብድር፣ ከመንግሥትና የግል አጋርነት ግዴታዎች፣ በፌዴራል መንግሥት ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ የክልል መስተዳድሮች ብድሮች እና ከሌሎች ተመሳሳይ ምንጮች የሚመነጩ የፊስካል ስጋቶችን የመለየት፣ የመገምገም፣ የመከታተልና የማስተዳደር ፖሊሲና ሥርዓት ያዘጋጃል፤ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የፊስካል ስጋት ግምገማ ያካሂዳል፤ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ፣ የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ እና የፊስካል ስጋት ፖሊሲዎችን ያወጣል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ የተጠቃለለ የፊስካል ስጋት መግለጫ በየዓመቱ ያቀርባል፤

8) ከተለያዩ መንግሥታት ጋር የሚደረገውን የሁለትዮሽ ኢኮኖሚ ትብብር እንዲሁም የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ከተቋቋሙ ዓለም ዓቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤ ትብብርና ትስስሩ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ የሚኖረውን ውጤት ይከታተላል፤

9) በፌደራል መንግስት፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች እና በማንኛውም የመንግስት ደረጃ የሚከናወኑ በመንግስትና በግል አጋርነት ማዕቀፍ የሚከናወኑ የመንግስት አገልግሎትና የመሠረተ ልማት ሥራዎች ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ እና የመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010 መሠረት

ውጤታማ እና ሀገራዊ መናበብ የሚፈጥሩ አሰራሮችን ይዘረጋል፤ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶችን ማስተካከያ እንዲደረግ ያደርጋል፤

10) የውጭ ዕርዳታና ብድር ያሰባስባል፣ ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

11) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

39. <u>የግብርና ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ግብርና እና የደን ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና የሕግ ማዕቀፎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ የአግሮፎረስትሪ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፤

2) ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች እና በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ የግል ዘርፍ ተዋንያን ተደራሽ የሆነ የግብርናና ገጠር ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤ የግብርናና ገጠር ፋይናንስ አገልግሎት እንዲጠናከር ጥናት ላይ የተመሠረተ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲወሰን ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

3) የግብርናና የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ትስስር ለማጠናከር ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ የሚመጣበትን ስልት ይነድፋል፤ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

4) የግብርና ምርምር ሥራዎች የዘርፉን ችግር የሚፈቱ መሆናቸውን እና እንደአስፈላጊነቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሰራታቸውን ያረጋግጣል፤ ያስተባብራል፤

5) የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራና ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በገበያ የሚቀርብ ማናቸውንም የሰብል ምርት፣ እንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

6) የግብርና ምርት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በንጥረ-ነገር ይዘቱ የበለፀገ የተሰባጠረና ጤናማነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሥርዓት መኖሩን ያረጋግጣል፤

7) የሰብል፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የምርት ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የግብርና ኤክስቴንሽን የምክር አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ እና አመራረት ስልቶች አቅርቦት እንዲስፋፋና አጠቃቀሙም እንዲያድግ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤ ተያያዥነት ያላቸው የተፈጥሮ ሃብት ልማት ግብዓቶች ፍላጎት፣ አቅርቦትና ስርጭት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

8) የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት ምዘገባና ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የምርት ጥራት፣ ጤናና ደኅንነት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡት የዕፅዋት ቁጥጥር እና እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦዎች ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ሥራን ያስተባብራል፤

9) የከተማ ግብርናን ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስልት ይነድፋል፤ የአተገባበር ሥርዓት ይዘረጋል፤

10) የቡናና የሻይ ልማት እና ግብይት ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ይከታተላል፤ ያስተባብራል፤

11) የዕፅዋት፣ እንስሳትና ዓሳ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

12) የእፅዋትና እንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤ አስፈላጊ መሠረተ-ልማቶች ይዘረጋል፤ ላብራቶሪዎችና ክሊኒኮች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ አቅማቸውን ይገነባል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

13) የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤ የሥጋና የወተት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በዘርፉ የሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምር በመለየት ወደ ገበያ የሚገቡበትን ሥርዓት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን የማደራጀትና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ሥራ ያስተባብራል፤ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ተዋጽኦ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ገበያ የሚተዋወቁበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፤

14) በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በገበያ የሚመራ የእንስሳት ሃብት ልማት፣ ውሃን ማዕከል ያደረገ የሰብልና የእንስሳት መኖ ልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የግጦሽ መሬት ልማት አጠቃቀም ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል፤

15) ለገጠር መሬት አስተዳደርና ለተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ዘላቂ የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤ ሀገር ዓቀፍመረጃ ያደራጃል፤

16) የተፋሰስ፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲሰፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤

17) በሕግ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም የተፈጥሮ ሀብት መመናመንና የአፈር መሸርሸር መንስኤዎችን ይለያል፤ የመከላከያ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤ የአፈር ለምነት የሚሻሻልበትን፣ የአፈር ጤንነት የሚጠበቅበትን እና ሀገራዊ የአፈር መረጃ ሥርዓትና የአፈር ምርምር ተግባር የሚከናወንበትን ስልት የመንደፍ ሥራን ያስተባብራል፤

18) የሀገሪቱን የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች በአግባቡ በማንበር፣ በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግና ፍትሃዊ የጥቅም ተጋሪነትን በማረጋገጥ ሀገሪቱና ህብረተሰቡ ከብዝሀ ሕይወትና ተያያዥ ነባር የማህበረሰብ ዕውቀት እንዲሁም ከሥርዓተ ምኅዳር አገልግሎቶች የሚያገኙት ጥቅም በዘላቂነት እንዲያድግ ድጋፍ ያደርጋል፤

19) ለግብርና የሚውል ውሃን ከዝናብ፣ ከገጸ-ምድር እና ከከርሰ-ምድር ምንጮች በማቀናጀት የውሃ ማቆር ሥራዎች፣ የወንዝ ጠለፋ፣ የምንጭ ማጐልበትና የውሃ መሣቢያ ሞተሮች አጠቃቀም የሚጠናከርበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤ የአርሶአደሩን እና አርብቶአደሩን የውሃ አጠቃቀም ክህሎት የበለጠ ለማሳደግ የድጋፍ እና ማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

20) የሰብልና እንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ በጥናት ግኝት ላይ የተመሠረተ ለቆላማ አካባቢዎች ግብርና ሥራዎች የሚውል የውሃ እና የመሬት አጠቃቀም እና የመስኖ ኤክስቴንሽን ሥርዓት ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የተገነቡ የመስኖ ግድቦች ለግብርና ልማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

21) የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ በግብርና ልማት ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ለመተንበይ የሚያስችል አቅም እንዲገነባ ድጋፍ ያደርጋል፤ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመቋቋም አቅምን ለማጠናከር የዕለት ደራሽ ድጋፍ እና የምግብ

ዋስትና የሚረጋገጥበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤ በገጠር የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤

22) የእንስሳት ልማት ኢንስቲቲዩትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 506/2014 ለኢንስቲትዩቱ የተሰጡ ከእንስሳት ምርምር ውጪ የሆኑ ሥልጣንና ተግባራት ለሚኒስቴሩ ተላልፈዋል፡፡

23) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ያከናውናል፡፡

40. <u>የጤና ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

የጤና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ጤናን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎችን ይቀርጻል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2) የጤናውን ዘርፍ ልማት ሀገራዊ ፕሮግራም ይነድፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

3) የጤና አገልግሎት ሽፋን ካርታ ያዘጋጃል፤ የጤና አገልግሎት ሽፋን እንዲያድግና የጤና መሠረተ-ልማቶች እንዲስፋፉ ድጋፍ ያደርጋል፤ የጤና ፕሮግራሞችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

4) የሀገሪቱን የጤና ችግር ለመፍታትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚረዱ ምርምሮች እንዲካሄዱ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

5) ሀገራዊ የሥርዓተ-ምግብ ስትራቴጂ አፈጻጸምን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

6) ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

7) የኅብረተሰቡን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን የመከላከል እርምጃ ይወስዳል፣ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የሌሎች አካላት ሥራዎችን በማስተባበር ለችግሩ አፋጣኝና ውጤታማ መፍትሄ ይሰጣል፤

8) አግባብነት ያላቸውን የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

9) በሀገሪቱ ውስጥ የአስፈላጊ መድሃኒቶችና የሕክምና መሣሪያዎች በቂ አቅርቦት መኖሩንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

10) የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ይከታተላል፤

11) የጤና ባለሙያዎችን እና የጤና ተቋማትን በተመለከተ የቁጥጥር ሥርዓት በአግባቡ መፈጸሙን ይከታተላል፤

12) በሀገሪቱ ውስጥ የሚሰጠው የጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ጥራትና አግባብነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፣ ያረጋግጣል፤

13) የባሕል ህክምና ከዘመናዊው ህክምና ጋር እንዲቀናጅና አሠራሩን ከዘመናዊው መድሀኒት ጎን ለጎን እንዲሰራ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ይሰራል፤

14) የፌዴራል ሆስፒታሎችን አስተዳደር በበላይነት ይቆጣጠራል፣ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች ማስተማሪያ ሆስፒታሎችን አቅም በማጎልበት ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤

15) ሀገራዊ የጤና መድን ሥርዓቱን ይመራል፤ አፈፃፀሙንም ይቆጣጠራል፤ ሀገራዊ የጤና መረጃ ሥርዓቱን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

16) በአዋጅ ቁጥር 276/1994 ለኤች.አይ.ቪ /ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፅህፈት ቤት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ ያውላል፡፡

17) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

41. <u>የፍትሕ ሚኒስቴር ሥልጣን እና ተግባር</u>

1) የፍትሕ ፖሊሲዎችን፣ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂ እና ሕጎችን ያመነጫል፡፡

2) የፍትሕ ሚኒስቴር በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ያውላል፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍትሕ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ባልተግባቡበት የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

ለ) በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የሚገኙ ከወንጀል ጋር የተገናኙ ንብረቶች የማስመለስ ሥራዎችን ይሰራል፣ ያስተባብራል፤

ሐ) የፌደራል ሕጎችን በመጣስ በተፈጸሙ ወንጀሎች ላይ የሚከናወኑ የምርመራ ሥራዎችን ሕጋዊነት ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤

መ) ታራሚዎችን የማረምና ማነጽ ሥራዎችን፣ በዘርፉ የሚደረጉ ጥናቶችንና የሚሰጡ ሥልጠናዎችን፣ ከግብር ጋር የተያያዙ የይግባኝ ሥራዎችን፣ የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ሥራዎችን፣ የጸረ-ሙስናና ሥነ ምግባር ጉዳዮች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን የሚመለከቱ ሥራዎችን ያስተባብራል፤

ሠ) የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቶችን አደረጃጀት እና የአሠራር ሥርዓት በጥናት ላይ ተመስርቶ በሕግ እንዲወሰን ያደርጋል፤

ረ) በግልግል ዳኝነት ወይም በሌላ አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች ላይ ለሚሰሩ አካላት ፈቃድ ይሰጣል፣ የመመዘኛ መስፈርት ያዘጋጃል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

ሰ) የፍትሕ መለኪያዎችን ወይም የፍትሕ አመላካች ሀገር ዓቀፍ ስታንዳርዶችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ያወጣል፤

ሸ) የፍትሕ የመረጃ ቋት ያለማል፤ ያስተዳድራል፤ የፍትሕ መረጃን ይተነትናል፤ ያሰራጫል

ቀ) በሌሎች ሕጎች ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል።

4) የፍትሕ ሚኒስትሩ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይሆናል፤

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>ስለ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት</u>

42. <u>ሌሎች አስፈጻሚ አካላት</u>

1) የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

ሀ) የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን፣

ለ) አውሮፕላን አደጋ ምርመራ ጽሕፈት ቤት፣

ሐ) ብሔራዊ የምርምር ፈንድ እና ምክር ቤት፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተቋቋሙ አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

3) በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 የተቋቁሙት የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ እንደተቋቋሙ ተቆጥረው አደረጃጀታቸውን እና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንቦች ወይም በአዋጁ መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን ይቀጥላሉ፡-

ሀ) የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣

ለ) የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት፣

ሐ) የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣

መ) የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት፣

ሠ) የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲቲዩት፣

ረ) ብሔራዊ የተሀድሶ ኮሚሽን ፤

ሰ) የትምህርት እና ሥልጠና ባለሥልጣን፣

ሸ) የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን፣

ቀ) የግብርና ገጠር ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት፣

በ) የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት፣

ተ) የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፣

ቸ) የአፍሪካ አመራር ልሕቀት አካዳሚ፣

ኀ) የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣

ነ) የኢትዮጵያ ሜትዮሮሎጂ ኢንስቲቲዩት

ኘ) የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን፣

አ) የኢትዮጵያ ቴክኒክ ልሕቀት ኢንስቲቲዩት፣

ከ) የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለሥልጣን፣

ኸ) የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት፣

ወ) የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን፤

ዐ) የኢትዮጵያ ደን ልማት፣

ዘ) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲቲዩት፣

ዠ) የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን፣

የ) የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን፣

ደ) የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ኢንስቲቲዩት፣

ጀ) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ታለንት ልማት ኢንስቲቲዩት፣

ገ) የእንስሳት ጤና ኢንስቲቲዩት፣

ጠ) የውጭ ጉዳይ ኢንስቲቲዩት፣

ጨ) የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት፣

፰) የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት፣

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱ እና አደረጃጀታቸው እና ሥልጣንና ተግባራቸው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያልተወሰነ አስፈጻሚ ተቋማት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ይወሰናል።

ክፍል ስድስት

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል እና በተጠሪ ተቋማት መካከል ስለሚኖር ግንኙነት እንዲሁም አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ስለማደራጀት

43. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል እና በተጠሪ ተቋማት መካከል ስለሚኖር ግንኙነት

1) ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ወይም ለሌላ አስፈጻሚ አካል ተጠሪ የሆነ ተቋም በሕግ የተቋቋመ ራሱን የቻለ ተቋም በመሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል የተጠሪ ተቋሙን ሥራዎች ከመምራት፣ ከማስተባበርና ከመደገፍ ውጪ በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴው ላይ ጣልቃ አይገባም።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወይም የሌላው አስፈጻሚ አካል ዕቅድና ሪፖርት የተጠሪ ተቋሙን ዕቅድና ሪፖርት ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

3) በሕግ በሚዘረጋ ሥርዓት መሠረት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወይም ሌላው አስፈጻሚ አካል የተጠሪ ተቋምን የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የፋይናንስ አስተዳደርና መሰል ሥራዎችን ሊያከናውን ይችላል።

4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም ተቋም "መምራት፣ ማስተባበርና መደገፍ" ማለት፡-

ሀ) የተጠሪ ተቋማትን ዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት አጠቃላይ አፈፃፀም መከታተልን፤

ለ) የተቋሙን አደረጃጀት እንዲሁም የልማት ሥራ ፕሮግራሞቻቸውን፣ ፕሮጀክቶቻቸውንና በጀቶቻቸውን መገምገምና ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ማቅረብን፤

ሐ) በሕግ የተሰጧቸውን ተግባርና ሀላፊነቶች በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ መደገፍን፤

መ) ከውጭ ሀገር ተቋማት ጋር ግንኙነት የሚፈጥሩበትን ሁኔታ ማመቻቸትና መደገፍን፤

ሠ) የተጠሪ ተቋማትን እና የተጠሪ ተቋማት ባለሙያዎችን አቅም መገንባትን ይጨምራል።

44. ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ አስፈጻሚ አካላት

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡-

1) የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት፣

2) የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፤

3) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣

4) የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣

5) የኢትዮጵያ የኒውክሊየር ኃይል ኮሚሽን፣

6) የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ፣

7) የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደር፣

8) የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት፣

9) የፋይናንስ ደኅንነት አገልግሎት፣

10) የአርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ ኢንስቲቲዩት፣

11) የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት፣

45. <u>ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይሆናል፦

1) የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣

2) የግል ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣

3) የኢትዮጵያ ተቀማጭ ገንዘብ ፈንድ፤

46. <u>ለመከላከያ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለመከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፦

1) የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣

2) ብሔራዊ የተሀድሶ ኮሚሽን።

47. <u>ለማዕድን ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለማዕድን ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲቲዩት፣

2) የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት፤

48. <u>ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ይሆናል፦

1) የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ኢንስቲቲዩት፣

2) የኢትዮጵያ የቴክኒክ ልህቀት ኢንስቲቲዩት፣

3) የግብርና ቴክኒክ፣ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች፣

4) የኢትዮጵያ ጎብረት ሥራ ኮሚሽን፤

49. <u>ለሰላም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሰላም ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን፣

2) የመንግሥታት ግንኙነት ማስተባበሪያ ሴክሬታሪያት፤

50. <u>ለባሕል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይሆናል፦

1) የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን፣
2) የኢትዮጵያ የዱር ሕይወት ባለሥልጣን፣
3) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት ባለሥልጣን፣
4) የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት፣
5) ብሔራዊ ቲያትር፤

51. <u>ለብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር ይሆናል፦

1) የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት፣
2) የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት፤
3) የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፤
4) የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣
5) የኢትዮጵያ መሶብ አገልግሎት፣
6) የአፍሪካ አመራር ልሕቀት አካዳሚ፣

52. <u>ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፦

1) የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች፣
2) የትምህርት ብቃት፣ ምዘናና ማረጋገጫ ባለሥልጣን፣
3) ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣
4) ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ፣
5) የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን፤

53. <u>ለሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ይሆናል፦

1) የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን፣
2) የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን፣
3) የመንገድ ደኅንነትና መድን ፈንድ ባለሥልጣን፣
4) የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ጽሕፈት ቤት፤

54. <u>ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲቲዩት፣

2) የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲቲዩት፣

3) የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣

4) የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት፣

5) የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን፤

55. <u>ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት፣

2) የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት፤

56. <u>ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለሥልጣን፣

2) የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን፣

3) የስፔስ የሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲቲዩት፣

4) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ታለንት ልማት ኢንስቲቲዩት፣

5) የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን፣

6) ብሔራዊ የምርምር ፈንድ እና ምክር ቤት፤

57. <u>ለከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት፣

2) የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን፣

3) የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፤

58. <u>ለወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣

2) የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን፤

59. <u>ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂካል ኢንስቲቲዩት፣

2) የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት፣

3) የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለሥልጣን፤

60. <u>ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የውጭ ጉዳይ ኢንስቲቲዩት፣

2) የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት፤

61. <u>ለገቢዎች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገቢዎች ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን፣

2) ብሔራዊ ሎተሪ አገልግሎት፤

62. <u>ለገንዘብ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገንዘብ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ፣

2) የመንግሥት ግዢ አገልግሎት፣

3) የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን፤

4) የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣

63. <u>ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለግብርና ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት፣

2) የግብርናና የገጠር ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት፣

3) የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን፣

4) የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን፣

5) የእንስሳት ጤና ኢንስቲቲዩት፣

6) የኢትዮጵያ ደን ልማት፣

7) የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲቲዩት፤

64. <u>ለጤና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጤና ሚኒስቴር ይሆናል፦

1) የኢትዮጵያ ብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት፣

2) የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት፣

3) የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲቲዩት፣

4) የኢትዮጵያ ጤና መድሕን አገልግሎት፣

5) የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት፣

6) የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን፣

7) ቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

8) ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣

9) አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

10) አለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

11) የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት፤

12) የኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል፤

65. <u>ለፍትሕ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፍትሕ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

1) የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፤

2) የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን፣

3) የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት፣

4) የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን፣

5) የሥነ-ምግባር እና ጽረ-ሙስና ኮሚሽን፣

6) የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት፣

66. <u>ለብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ተጠሪ የሆኑ አካላት</u>

የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ተጠሪነት ለብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ይሆናል፡፡

ክፍል ሰባት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

67. የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ስለማቋቋም

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሩን ለማስፈፀም የሚያግዙ ከሚኒስቴር ውጪ ያሉ ሌሎች አስፈጻሚ አካላትን በደንብ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

68. ስለምርምር ኢንስቲቲዩቶች

1) የሀገሪቱን የጥናትና ምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የኢኖቬሽን፣ የኢንተርፕረነርሺፕ ወይም የገበያ ማዕቀፍ ልማት ግቦችን ለማሳካት በዚህ አዋጅ የተቋቋሙ ኢንስቲትዩቶች በሰው ሃብት አስተዳደር፣ በፋይናንስ አስተዳደር እና የገቢ አሰባሰብ ላይ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

   ሀ) የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁጥር 1353/2017 መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል የጥናትና ምርምር ባለሙያዎችን፣ ሳይንቲስቶችን እና የቴክኒክ ባለሙያዎችን ለመቅጠር፣ ለማስተዳደር፣ ለማሰናበት፣ የደመወዝና ጥቅማጥቅም ስኬል ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ አዘጋጅተው ተቋሙ ተጠሪ ለሆነለት አካል በማቅረብ ያፀድቃሉ።

   ለ) የፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ቢኖርም ተቋማቱ በማቋቋሚያ ሕጋቸው መሠረት ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች፣ ከወጪ መጋራት፣ ከልማት አጋሮች ከሚሰበሰቡ ፈንዶች የሚያገኙትን ገቢ የመሰብሰብ እና ለተልዕኳቸው ዓላማ መልሶ የመጠቀም ሥልጣን ይኖራቸዋል።

2) ተቋማቱ የሚከተሉት የሒሳብ አያያዝ እና የግዥ አሠራር አጠቃላይ ዓለም ዓቀፍ የሒሳብ አያያዝ ስታንዳርድን እና ተወዳዳሪ የንግድ አሠራርን በተከተለ ሁኔታ መተግበር ያለበት ሆኖ የግዥና ፋይናንስ መመሪያቸው ተቋሙ ተጠሪ በሆነለት አካል መጽደቅ አለበት።

69. የስያሜ ለውጥ ስለተደረገባቸው አስፈጻሚ አካላት

የሚከተሉት ተቋማት የስያሜ ለውጥ ተደርጎባቸዋል፡-

1) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲቲዩት የነበረው ስያሜ "የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲቲዩት" በሚል ተቀይሯል፤
2) የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲቲዩት የነበረው ስያሜ "የኢትዮጵያ የቴክኒክ ልሕቀት ኢንስቲቲዩት" በሚል ተቀይሯል፤
3) የዱር እንስሳት ባለሥልጣን የነበረው ስያሜ "የዱር ሕይወት ባለሥልጣን" በሚል ተቀይሯል፤
4) የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት የነበረው ስያሜ "የግብርናና የገጠር ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት" በሚል ተቀይሯል፤
5) የመንገድ ደኅንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት የነበረው ስያሜ "የመንገድ ደኅንነትና መድን ፈንድ ባለሥልጣን" በሚል ተቀይሯል፤

6) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ-መዛግብት እና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት የነበረው ስያሜ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ-መዛግብት እና ቤተ-መጻሕፍት ባለሥልጣን" በሚል ተቀይሯል።

7) የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት የነበረው ስያሜ "የትምህርት ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ባለሥልጣን" በሚል ተቀይሯል።

70. <u>በመንግስት ባለቤትነት ስለተያዙ የልማት ድርጅት</u>

በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ፣ የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ እና የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ግሩፕ በፌዴራል መንግስት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1314/2017 መሠረት እንደተቋቋሙ ተቆጥረው ሥራቸውን ይቀጥላሉ::

71. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

1) የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014፤

2) የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 244/2003፤

3) የቤተ መንግሥት አስተዳደርን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 459/1997፤

72. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ድንጋጌዎች</u>

የሚከተሉት ሕጎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡-

1) የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን መቋቋም የሚመለከተው አንቀጽ 3፤

2) የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ተጠሪነትን የሚመለከተው አንቀጽ 3(2)፤

3) የመንገድ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 66/1989፣ የመንገድ ፈንድ ፅህፈት ቤት መቋቋምና አደረጃጀት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

4) የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 268/1994፣ የውሃ ልማት ፈንድ ፅህፈት ቤት መቋቋምና አደረጃጀት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

5) የኢትዮጵያ ብቃትና ሥራ አመራር ኢንስቲቲዩትን የሚያቋቁመው የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 ኢንስቲትዩቱን መቋቋምና አደረጃጀትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

6) የእንስሳት ልማት ኢንስቲቲዩትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 506/2014፤

7) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀጽ 43(3)፤

8) የኢትዮጵያ የብቃትና ሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት አደረጃጀት፣ሥልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 584/2018 አደረጃጀትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

9) የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ምክር ቤት እና ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 388/2008 የኢንስቲትዩቱን መቋቋም እና አደረጃጀት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

10) የብሔራዊ ሎተሪ አገልግሎት (ስያሜው በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እንደተሻሻለ) እንደ ገና ለማቋቋም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5)፤

11) በኢትዮጵያ የአውሮፕላን አደጋና የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ አዋጅ ቁጥር 957/2008 የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ቢሮ መቋቋምና አደረጃጀትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

12) ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

73. <u>የሥልጣንና ተግባራት መተላለፍ</u>

1) በቤተ መንግሥት አስተዳደርን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 459/1997፣ እንዲሁም በቤተ መንግሥት አስተዳደር ለመደንገግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 552/2016 ላይ ለአስተዳደሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ተላልፈዋል።

2) በኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ምክር ቤት እና ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 388/2008 መሠረት ለኢንስቲቲዩት ተሰጥተው የነበሩ፡-

   ሀ) ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት ለአርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል፤

   ለ) ከግብርና ጋር ተያያዥነት ያላቸው ባዮ ቴክኖሎጂን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት ለግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት እንዲሁም ከጤና ጋር ተያያዥነት ያላቸው ባዮ ቴክኖሎጂን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት ለአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል።

3) የደን እና የእንስሳት ምርምርን በሚመለከት በሌላ ሕግ ለሌላ አስፈጻሚ አካል የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በደንብ ቁጥር 527/2015 ለተቋቋመው የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል።

4) በፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 አንቀጽ 20(1) መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የብቃትና ሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የአፍሪካ አመራር ልሕቀት አካዳሚ ተላልፈዋል።

5) በኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1075/2010 አንቀጽ 6 (ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3) እንዲሁም አንቀጽ 8 (ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3) መሠረት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን የመመዝገብ፣ መዝገብ የመያዝ፣ የዓመት ሪፖርቶችን የመቀበልና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከማለፉ በፊት የማወቅ ሥልጣንና ተግባራት ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት ለአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ተሰጥተዋል።

6) የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 507/2014 አንቀጽ 5(7) ስር ለቴክኖሎጂ ባለሥልጣን የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ለአከባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ተሰጥቷል።

7) በኢትዮጵያ የአውሮፕላን አደጋ እና የአደጋ ኢ*ጋ*ጣሚ ምርመራ አዋጅ ቁጥር 957/2008 ለአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ቢሮ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ጽሕፈት ቤት ተላልፏል።

8) በሀገር ዓቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 260/2004 የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ የትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማረ*ጋ*ገጫ ማዕቀፍ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 561/2017 ሥር የተቀመጡ ሥልጣንና ተግባራት ለትምህርት ብቃት ምዘናና ማረ*ጋ*ገጫ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥተዋል።

9) በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 35፣ 36 እና 37 ሥር ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለሰላም ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

10) በሌሎች ሕጎች የተቋቋሙና ስያሜያቸው በዚህ አዋጅ የተሻሻለ አስፈጻሚ አካላት ስያሜያቸው በዚህ አዋጅ በተገለፀው አግባብ ተሻሽሎ በተቋቋሙበት ሕግ እና እንደአግባብነቱ በሌሎች ሕጎች መሠረት የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባራት ማከናወናቸውን ይቀጥላሉ::

74. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

1) የቤተ መንግሥት አስተዳደር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ተላልፈዋል፤

2) የቱሪዝም ሚኒስቴር እና ባሕልን የሚመለከቱ የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

3) ወጣቶችን የሚመለከቱ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ስፖርትን የሚመለከቱ የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

4) የፕላንና ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

5) የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

6) የእንስሳት ልማት ምርምርን ከሚመለከቱ ጉዳዮች ውጪ የሆኑ የእንስሳት ልማት ኢንስቲቲዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የግብርና ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

7) የደን ምርምርን የሚመለከቱ የኢትዮጵያ ደን ልማት መብትና ግዴታዎች ለግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል፤

8) የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃን የሚመለከቱ የፍትሕ ሚኒስቴር እና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን ተላልፈዋል፤

9) የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የትምህርት ብቃት፣ ምዘናና ማረ*ጋ*ገጫ ባለሥልጣን ተላልፈዋል፤

10) የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲቲዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ የቴክኒክ ልህቀት ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል፣

11) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲቲዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል፤

12) ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂን የሚመለከቱ የባዮ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል፤

13) ግብርናን የሚመለከቱ የባዮ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት መብትና ግዴታዎች ለግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል፤

14) ጤናን የሚመለከቱ የባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት መብትና ግዴታዎች ለአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል፤

15) የኢትዮጵያ ብቃትና ሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ለአፍሪካ የአመራር ልህቀት አካዳሚ ተላልፈዋል፤

16) የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

17) የመንገድ ፈንድ ጽሕፈት ቤት መብትና ግዴታዎች ለከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

18) የውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት መብትና ግዴታዎች ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

19) በኢትዮጵያ የአውሮፕላን አደጋና የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ አዋጅ ቁጥር 957/2008 የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ጽሕፈት ቤት ተላልፏል።

20) በሀገር ዓቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 260/2004 የኤጀንሲው መብትና ግዴታዎች ለትምህርት ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ባለሥልጣን ተላልፏል።

75. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1) የሕጎችን ተፈፃሚነት የሚያስቀሩ፣ እና ሥልጣንና ተግባርን እንዲሁም መብትና ግዴታዎችን የሚያስተላልፉ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 72 [9]፣ 73[6] እና 74 [7፣8፣እና 18] ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት እነዚህን ድንጋጌዎች የሚመለከቱ በዚህ አዋጅ አንቀፀ 42[1][ሀ፣ለ እና መ] የተቋቋሙ አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀቱ ሥልጣንና ተግባር የሚወስን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ወጥቶ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

2) በተለያዩ ሕጎች ተቋቁመው ሥልጣንና ተግባራቸው በአንድ ተቋም ስር እንዲመጣ የተደረገ እንደሆነ የተቋሙን አደረጃጀት እንዲሁም ሥልጣንና ተግባራት የሚደነግግ ሌላ ሕግ እስከሚወጣ ድረስ ወደ አንድ የተጠቃለሉት ተቋማት በተቋቋመበት ሕግና በሌሎች ሕጎች ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራትን ማከናወኑን ይቀጥላሉ::

3) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 70 ድንጋጌ ቢኖርም፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂካል ኢንስቲቲዩት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር የሚወስን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እስከሚወሰን ድረስ የአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 72 ሥር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ያከናውናል።

ለ) የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር የሚወስን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እስከሚወሰን ድረስ የቤተ መንግሥት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 552/2016 ላይ ለአስተዳደሩ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ጽሕፈት ቤቱ ያከናውናል።

76. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2) ማንኛውም አስፈጻሚ ተቋም በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ የተሰጠውን ግልጽ ተግባርና ኃላፊነት ለማስፈፀም የሚያስፈልግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

77. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ

መስከረም ———— ቀን 2019 ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዝዳንት